# ጋዜጣዊ መግለጫ

## የግሬት ሪፍት ቫሊ አኖቬሽን ሰሚት

### የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ የግሬት ሪፍት ቫሊ የኢኖቬሽን ሰሚት ይፋ አደረገ

ግሬት ሪፍት ቫሊ ኢኖቬሽን ሰሚት/ጉባዔ የ2017 የመጀመሪያው ጉባዔ የፈጠራ ሥራዎችን በገንዘብ ድጋፍ ለማጎበዝ ያለመ ሲኾን በግብርና፣ በጤና እና በትምሕርት ላይ ለሚሠሩ ስታርትአፖች $750,000 የአሜሪካ ዶላር በሽልማት መልክ አዘጋጅቷል

**ጉባዔው ከጥር 23 2017 – ጥር 24 2017 በስካይላይት ሆቴል ይከናወናል**

---

**አዲስ አበባ -- ኢትዮጵያ**

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ በዐይነቱ የተለየውንና የፈጠራ ሥራዎችን ለማጎልበት ያለመውን የግሬት ሪፍት ቫሊ ኢኖቬሽን ሰሚት አዘጋጀ። የዚህ ጉባዔ መክፈቻ በስካይላይት ሆቴል ከዓርብ ጥር 23 2017 – ቅዳሜ ጥር 24 2017 የሚካኼድ ሲኾን በአፍሪካ ትልቁ የስታርትአፕ የገንዘብ ድጎማ ይፋ ይደረጋል። በዚህም፤ በግብርና፣ በጤና እና በትምሕርት ዘርፍ የማኅበረሰብ ልማትን ለሚያፋጥኑ የላቁ የፈጠራ ውጤቶች $750,000 የአሜሪካ ዶላር በሽልማት መልክ ይበረከታል።

የግሬት ሪፍት ቫሊ ኢኖቬሽን ሰሚት/ጉባዔ በግብርና፣ ጤና እና ትምሕርት ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕርነሮች ሀገር-በቀልና ሀገር-ተኮር የፈጠራ ሐሳቦቻቸውን በገንዘብ ድጋፍ እንዲያሳድጉ፣ ሙያዊ ድጋፍ እንዲያገኙና ከኢንዱስትሪው ተዋናዮች ጋር እንዲተዋወቁ የሚያመቻች መድረክ ነው። ሉሊት እጅጉ፤ የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ ሊቀመንበር፤ ጉባዔው አዲስ ምዕራፍ የሚከፍት መኾኑን አመላክተው፣ ወደፊት ስለሚያመጣው በጎ ለውጥ አስመልክተው በሰጡት አስተየየት … "ይህ የፈጠራ ውድድርና በመቶ ሺዎች የአሜሪካ ዶላር የሚገመት ሽልማት አሸናፊዎችን የሀገር ምሰሶ በሆኑት ዘርፎች ማለትም በጤና፣ በግብርና እና በትምሕርት ዘርፍ ያሉ ተግዳሮቶችን ለመፍታት መላ እንዲፈጥሩና ችግር እንዲፈቱ ያስችላቸዋል። ጂ.አር.ቪ.አይ.ኤስ. በአፍሪካ አሕጉር ካሉት ትልልቅ የስታርትአፕ ጉባዔዎች አንዱ የሚኾን ሲኾን ተጠቃሽ ተጽእኖ እንደሚኖረው ታምኖበታል። አፍሪካ-መር እና አፍሪካ-አደግ መርሆን በመከተል ግሬት ሪፍት ቫሊ ኢኖቬሽን ሰሚት/ጉባዔ የአፍሪካ የፈጠራና የንግድ ሥራ ተግባርን ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋግራል።" ሲሉ ተደምጠዋል።

ጉባዔው የፓነል ውይይቶች፣ ወርክሾፖች፣ ኤግዚቢሽን እና ከኢንዱስትሪ ባለድርሻዎች ጋር የትውውቅ መድረክ የተዘጋጁበት በመኾኑ ተሳታፊዎች ልምድ እንደሚቀስሙበትና ተጠቃሚ እንደሚኾኑበት ይታመናል።

ግሬት ሪፍት ቫሊ ኢኖቬሽን ሰሚት/ጉባዔ ለፈጠራ ባለሙያዎች አስቸኳይ ጥሪ ያቀርባል። ሉሊት እጅጉ ይህን ጥሪ ሲያጠናክሩ … "በዓለማችን የሥራ ፈጠራና የሥራ ፈጣሪዎች ቁጥር እያደገ መምጣቱን እየተመለከትን ነው። እነዚህ ሥራ ፈጣሪዎች ልባምና ለስኬት የተዘጋጁ ሲኾኑ ዓላማቸውን ለማሳካት የሚሹት ትክክለኛ ድጋፍ በትክክለኛ ሰዓት ነው። እኛም እንደ ኢ.ዲ.ቲ.ኤፍ. ገንዘብ፣ ጊዜ፣ ያለንን ትስስር እና ዕምነታችንን በሀገር በቀል ፈጠራዎችና ፈጣሪዎች ላይ ጥለናል። በዚሁ አጋጣሚ ተስፋ ሰጪ የፈጠራ ሐሳብ ባለቤቶች ለውድድር እንድታመለክቱ፣ አጋሮች ድጋፍ እንድታደርጉ ጥሪ እናስተላልፋለን። ተባብረን፣ ተረባርበን ታሪክ እንሥራ።" ሲሉ አክለዋል።

EDTF

ለዓመታት፣ ኢ.ዲ.ቲ.ኤፍ. የኢትዮጵያን ዳያስፖራ በሀገር ውስጥ ከሚደረጉ የልማት ሥራዎች ጋር በማስተሳሰር የበኩሉን የአመቻችነት ሚና ሲጫወት ቆይቷል። አሁን ደግሞ በግሬት ሪፍት ቫሊ ኢኖቬሽን ሰሚት/ጉባዔ የተወሳሰቡ ማኅበራዊ ተግዳሮቶችን ለመቅረፍ የኢንተርፕርነርሺፐን ሚና በመረዳት የፈጠራ ሥራዎች እንዲያብቡ ለማገዝ ያለውን ቁርጠኝነት ይበልጥ ያጠናክራል።

**የገንዘብ ድጋፍ ዐይነቶች**

- **ሌጋሲ ቢዩልደር** (legacy Builder) **አዋርድ የተመደበው -- የማበረታቻ ሽልማት መጠን -- $650,000 የአሜሪካ ዶላር**

ኢንተርፕርነሮች $650,000 የአሜሪካ ዶላር ለመቀራመት በፈጠራ ሐሳብ ይፎካከራሉ። ይህ በምርጫው ሕዝብ የሚሳተፍበትንና $50,000 ሺሕ የአሜሪካ ዶላር ሽልማት የሚያስገኘውን **ፒፕልስ ቾይስ አዋርድ** ይጨምራል። **ሌጋሲ ቢዩልደር አዋርድ** ኢ.ዲ.ቲ.ኤፍ. በሚያተኩርባቸው የልማት ዘርፎች አወንታዊ አበርክቶ ሊኖራቸው የሚችሉ አዳዲና ዘላቂ የፈጠራ እና የንግድ ሥራዎችን ለማጎልበት ያለመ ነው።

    - **ዋና ሽልማት**: **$150,000 የአሜሪካ ዶላር**
    - **ፒፕልስ ቾይስ አዋርድ**: **50,000 የአሜሪካ ዶላር**

- **ወጣት የፈጠራ ሰው ሽልማት /ያንግ ኢኖቬተር አዋርድ ( young innovation Award ) -- የተመደበው የማበረታቻ ሽልማት መጠን -- $100,000 የአሜሪካ ዶላር**

በዚህ ምድብ ዕድሜያቸው ከ25 ዓመት በታች የኾኑ በላቀ ውጤት የተመረጡ ዐሥር ወጣት ሥራ ፈጣሪዎችና የጀማሪ ስታርትአፕ አንቀሳቃሾች የፈጠራ ሥራዎቻቸውን የማደግ ዓቅም ያጎለብቱበት ዘንድ እያንዳንዳቸው $10,000 የገንዘብ ሽልማት ያሸንፋሉ። ይህ ሽልማት ለወጣት ኢትዮጵያውያን ሥራ ፈጣሪዎች እና ኢኖቬተሮች ዕውቅና ለመስጠትና ትጋታቸውን ለማጎልበት ያለመ ነው።

ኢ.ዲ.ቲ.ኤፍ. ይህ ልዩ ጉባዔ የታለመለትን የኢትዮጵያን የፈጠራ ሥራ የማጎልበት ዓላማ ያሳካ ዘንድ ከተባበሩት መንግሥታት የልማት ፕሮግራም (ዩ.ኤን.ዲ.ፒ.) ጋር በመተባበር የሪቭት ቫሊ ኢኖቬሽን ሰሚት/ጉባዔ እና የፈንድንግ ውድድሩ ከማመልከት እስከ ልየታ እና ዳኝነትና አሸናፊዎችን የማሳወቅ ኺደት ግልጽ እና በከፍተኛ ትኩረት የሚከናወን ለመኾኑ ማረጋገጫ ይሠጣል።

**አመልክቱ**

በግብር፣ በጤና እና በትምሕርት ዘርፎች ልዩ ፈጠራ ያላችሁ ኢንተርፕርነሮችና ሥራ ፈጣሪዎች፣ የስታርትአፕ አንቀሳቃሾች ይህን ዌብሊን https://www.grvsummit.com በመጠቀም የመወዳደሪያ ሐሳባችሁን እስከ እሁድ, **ታኅሣሥ 9 2017 ዓ.ም. ድረስ** እንድታስገቡ ይሁን።

**ስለ ኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ**

EDTF

**የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ትረስት ፈንድ** በውጪ ሀገራት በሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተመሠረተ እና በኢትዮጵያ ልማት ላይ የበኩሉን አወንታዊ ሚና ለመጫወት የተቋዋቋዋመ ዓለማቀፍ ድርጅት ነው። ኢ.ዲ.ቲ.ኤፍ. የኢትዮጵያ ዳያስፖራ በሀገር ውስጥ የሚከናወኑ ማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸው ዘላቂ የልማት ሥራዎች እንዲደግፉና ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንደ ግሬት ሪፍት ቫሊ ኢኖቬሽን ጉባዔ የመሳሰሉ ማዕቀፎችንና መድረኮችን በመፍጠር ለብሩኅ ነገ ይሠራል።

ለበለጠ መረጃ ... ለጥያቄዎቻችሁ ... ወይም ቃለ መጠይቅ ለማድረግ በኢሜይል አድራሻችን
info@grvsummit.com መልዕክት ይላኩልን